abookmedwirchibtdpress.com

13/ <u>ተጠሪነት</u>

1/ የአካዳሚው ተጠሪነት ለሐረሪ ብሔራዊ ጉባኤ ይሆናል።

2/ የቦርዱ ሊቀመንበር ተጠሪነት ለጉባኤው ይሆናል።

3/ የሥራ አስኪያጁ ተጠሪነት ለቦርዱና ለጉባኤው ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ይሆናል።

4/ የካውንስሎቹ ተጠሪነት ለአካዳሚው ሥራ አስኪያጅ ይሆናል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

14 <u>ደንብ የማውጣት ሥልጣን</u>

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊው ደንብ በቦርዱ ረቆ ከተዘጋጀ በኋላ በጉባኤው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ጸድቆ ይወጣል።

15/ <u>ቅጣት</u>

ይህን አዋጅ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በተላለፈ ማንኛውም ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረት ይቀጣል።

16/ <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የክልሉ ነዋሪ፤ መንግሥታዊ ድርጅት ወይንም የፖለቲካ ፓርቲ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት።

17/ <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚፃረር ማንኛውም ሕግ ይህን አዋጅ በተመለከተ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የለውም።

18/ <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በሐረሪ ነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ኅዳር 14 ቀን 1991 ዓ.ም

<u>ሐረር</u>

አብዱላሂ ኢድሪስ

የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ

መንግሥት

ፕሬዝዳንት